# የግማሽ ዓመት /6 ወር/ ሪፖርት

## ቁልፍ ውጤቶች፡-

<u>ቁልፍ ውጤ ቶች</u>

- ለ30 የጽ/ቤት ኃላፊዎችና ም/ኃላፊዎች በለውጥ አመራር(change management) ላይ የተሠጠ ሥልጠና፤
- መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ(BPR) በ6 መ/ቤቶችና 2 ማዘጋጃ ቤት ተግባራዊ ሲደረግ የአፈፃፀም ሂደቱን በተመለከተ በመምራትና በማጠናከር የተሰጠ ድጋፍ፤
- በ32 የገጠር ቀበሌዎች ተግባራዊ የተደረገ የመልካም አስተዳደር ፖኬጅ፤
- በፍትህ ሥርዓትና እና በሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ሥራዎች ዙርያ 24 ጊዜ የተደረገ ድጋፋዊ ክትትልና 4 ጊዜ የተደረገ ውይይትና ግምገማ፤
- የመ/ቤቱንና የሴክተር መ/ቤቶች ስትራቴጂክ ዕቅድና ዓመታዊ የተቋም ዕቅድ ዝግጅት አስመልክቶ የተደረገ መከታተል፤
- በዕቅድ እንዲመራ የተደረገ የሰው ኃይል ልማት፤
- የተጠናከረና የተደራጀ ወረዳ አቀፍ መረጃ፤
- ደህንነታቸው ተጠብቆ አገልግሎት መስጠት የቻሉ የቪዲዮ ከንፍረንስግ ማሽኖችና ተዛማች ዕቃዎች፤
- የሰው ሀይል አስተዳደር በደረጃ ዕድገት ማቴሪያል በማሟላትና የመረጃ አያያዝ በማሻሻል ፈጣን ቀልጣፋና ብቃተ ያለው አገልግሎተ እንዲሰጥ የተደረገ ዘመናዊ የጽ/ቤት አደረጃጀት፤

## <u>የተፈፀሙ ዝርዝር ቁልፍ ውጤቶች</u>

- ለ30 የጽ/ቤት ኃላፊዎችና ም/ኃላፊዎች ሥልጠና ለመስጠት የሚያስፈልጉ የሥልጠና በጀት ዕቅድ ታውቋል፤የሥልጠና ርዕስ ተመርጦ ማኑዋል ተዘጋጅቶ ይገኛል፡፡
- ሥልጠና የሚሰጥ ባለሙያ ተጋብዞ ሥልጠናውን የሚሰጥበት አመቺ ጎዜ ክትትል በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡
- መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ ጥናት ሙሉ ትግበራ ለማድረጉ ለ6 መ/ቤቶችና 2 ማዘጋጃ ቤት ተከታታየ የሆነ ድጋፍ ከመደረጉም በተጨማሪ ስለ አስፈላጊነቱና አተገባበሩ ላይ የተወሰነ ግንዛቤ ሊያስጨብጥ የሚችል የዳሰሳ ጽሁፍ ተዘጋጅቶ ተላልፏል፤ ጽ/ቤቱ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት የመፍተሄ አማራጮች አስተግባር ግብረ-ኃይሉን በሰሳቢነት በመምራት የተጠኑ የሥራ ሂደቶች በሚተገብሩባቸው መ/ቤቶችና ደጋፊ የሥራ ሂደቶችን የሚተገበሩ መ/ቤቶች ደረጃ ከተከናወነው ድልድል ሳይታቀፉ የቀሩ 17 ተንሳፋፍ ሠራተኞች ድልድል እና ሌሎች አቤቱታዎችን ተቀበሎ ደንቡ በሚያዘው መሠረት እየታየ ምደባ እንዲሰጣቸው አድርጓል፡፡ በመጨረሻም በድልድሉ ያለተካተቱ የ60 ሠራተኞች ዝርዝር ሲተላለፍ በሰው ኃይል ያልተሸፈነ የ170ክፍት ሥራ ሂደቶች መረጃ ተሰብስቦ በማጠናቀር ተላልፏል፡፡ ለተቀሩና ቀጥሎ ለሚተገብሩ ለ10 መ/ቤቶችም ስለመሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የማስተዋወቅ ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡

- ለ346 የገጠር ቀበሌ አመራሮች በመልካም አስተዳደር ፖኬጅ ላይ የ3 ቀን ሥልጠና ከተሰጠ በኋላ የመልካም አስተዳደር ፖኬጅን ተግባራዊ ስለማድረጋቸው በ22 ቀበሌዎች በመገኘት ስለአሠራራቸው፣ስለአደረጃጀታቸውና ስለሥራ እንቅስቃሴያቸው በተመለከተ ግምገማና ውይይት በማድረግ ድጋፋዊ ክትትል ከመደረጉም በተጨማሪ ቅድመ መረጃ የማሰባሰብ ሥራ ተሰርቷል፡፡በልዩ ወረዳው ባሉ 16 መ/ቤቶችና በተሜቱ 13 የገጠር ቀበሌዎች በመገኘት የምርጥ ተሞክሮ መረጃ በመሰብሰብ ተጠናቅሮ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡
- በፍትህና በሲቪል ሰርቪስ መ/ቤቶች የዘመኑን የውጤት ተኮር ዕቅድ አዘጋጅተው ከሠራተኞ ጋር በመፈራረም ወደ ተግባር ስለመግባታቸውና የዕቅድ አፈፃፀማቸውን በማሻሻል አዳዲስ አሠራሮችን ተከትለው እየሠሩ ለመሆኑ 12 ጊዜ በተደረገ ክትትል ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡
- በተደረገው ተከታተይ ክትትል ከግብርና ልማት ጽ/ቤት በስተቀር ሌሎች 15 መ/ቤቶች የ2001 ዓ.ም ዕቅዳቸውን አቅርበዋል፡፡
- ከ15ቱ ጽ/ቤቶች ተዘጋጅቶ የቀረበው የ2001 ዓ.ም የተቋም ዕቅድ የዕቅድ ስልትን በተከተለ የተዘጋጀ ስለመሆኑ በዝርዝር ተጣርቶ ግብረ-መልስ ተሰጥቷቸዋል፡፡
- በተሰጠው ግብረ-መልስ መነሻነትም የንግድና ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ልማት ጽ/ቤት፣የአስተዳደር ጽ/ቤት፣የውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት የማሻሻያ ወይም የማስተካከያ ዕቅድ አዘጋጅቶ ሲቀርብ የታክስ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ከፍተኛ ፍ/ቤት እና ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት በአሠራር ላይ ይታይ የነበረውን የግንዛቤ ማነስ ችግር ለማስወገድ በግንባርም ቀርቦ በመወያየት መረዳዳት ተደርጓል፡፡
- ከ16 ሴክተ መ/ቤቶች አጠቃላይ የወረዳው የሰው ኃይል መረጃ ተሰብስቦ ከመደራጀቱም በተጨማሪ በልዩ ወረዳው ባሉ ጽ/ቤቶች ከተፈቀዱ የሥራ መደቦች መካከል በሰው የተያዙና ያልተያዙ የሥራ መደቦች ብዛት ተለይቶ ታውቋል፡፡
- የቪዲዮ ኮንፍረንሲንግ ማሽኖችና ተዛማጅ ዕቃዎች ደህንነታቸው ተጠብቆ አገልግሎት በመስጠት እየተሰራበት ይገኛል፡፡
- የጽ/ቤቱ የሰው ሀይል መረጃ በኮምፒዩተር ተዘጋጅቶ በዘመናዊ መልክ ተደራጅቶ ይገኛል፡፡መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጡን ተግባራዊ ከማድገግ አንፃር ለተፈቀዱ የሥራ ሂደቶች ጽ/ቤት ከሞላ ጎደል በመመቻቸት ላይ የሚገኝ ሲሆን ለሥራ ሂደቱ የሚያፈልገው ማቴሪያልም በየደረጃው እየተሟላ ይገኛል፡፡

## <u>የተፈፀሙ ዝርዝር አበይት ውጤቶች</u>

- በ9 ካቢኔ መ/ቤቶችና በ2 ሌሎች መ/ቤቶች የሪፎሙ ይዘት ጠቀሜታና አስፈላጊነት በእምነት እንዲያዙ 12 ጊዜ ከኃላፊዎች፣ከም/ኃላፊዎችና፣ ከሠራተኞች ጋር ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል፡፡
- የሚፈልጉ የአሠራር መመሪያዎች በ22 የገጠር ቀበሌዎች ተደርሶ እየተሰራበት ስለመሆኑ ክትትል ውይይትና ግምገማ ተካሄዷል፡፡
- በ9 ካቢኔ መ/ቤቶችና በ7 ሌሎች መ/ቤቶች ስለሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያና ፈትህ ሥርዓት ማሻሻያ ንዑስ ፕሮግራሞች አተገባበር አስመልክቶ 12 ጊዜ ክትትል ግምገማ ውይይት በማድረግ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡
- በፍትህ ሴክተር ስለመሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ ትግበራ በሚመለከት 5 ጊዜ እና በማረምያ ቤት 1 ጊዜ በድምሩ 6 የማስተዋወቅ ሥራ በመሥራት ግንዛቤ በማስጨበጥ ወደ ተግባር እንዲገባ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

- በ12 ሴክተር መ/ቤቶች የቀረበው የ2ኛ ሩብ ዓመት ዘገባ በዕቅዳቸውና በሪፖርት ማቅረብያ ፎርማት መሠረት የተዘጋጀ ለመሆኑ በዝርዝር ግምገማ ተደረጎ ግብረ-መልስ ተሰጥቷቸዋል፡፡
- በመለስተኛ መሣሪያዎች አጠቃቀም ላይ በፎሩ ማዘጋጃ ቤት፣በፋ/ኢ/ልማት ጽ/ቤት በሣጃ ማረም ቤት፣በግብርናና ገጠር ልማት ጽ/ቤት እና በማስታወቂያና ባሕል ጽ/ቤት የኮምፒዩተርና የፐርንተር ጥገና በማድረግ 12 ማሽኖች አገልግሎት እንዲሰጡ የሙያ ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- የጽ/ቤቱን ዝርዝር የሥራ ዕቅድ መነሻ ያደረገ የበጀት የዕቅድ ቢቀርብም ካለው የበጀት ማነስ አንፃር ለጽ/ቤቱ የተፈቀደውን የዘመኑን በጀት በመደልደል አብቃቅቶ የመሥራት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡
- ሥራ ላይ እንዲውሉና ስለመዋላቸው ታውቆ እንዲፈፀም የሚላኩ ልዩ ደንቦችና መመሪያዎችነ አዋጆች ሥራ ላይ ከመዋላቸው በተጨማሪ ለመረጃነት ተደራጅተው የተቀመጡ ሲሆን ተባዝቶ ለሠራተኞችና ለሴክተር መ/ቤቶች በመሰራጨት እየተሰራበት ይገኛል፡፡
- ከመ/ቤቱ የወጡ 132 የወጪና የተለያየ መ/ቤቶች የመጡ 237 የገቢ ደብዳቤዎች ስርጭት ወቅቱን በጠበቀ ተከናውኗል፡፡

<u>የዕቅድ አፈፃፀም ደረጃ በመቶኛ</u>

ቁልፍ ውጤቶች <u>80.04%</u>
ዐበይት ውጤቶች <u>79.69%</u>

## <u>ማ ጠ ቃ ለ ያ</u>

- በየመ/ቤቱ እየታየ ያለው የሥራ ተነሳሽነት ከበፊቱ የተሻለ ቢሆንም የተሻለ ለውጥ ለማምጣት የሚመለከተው ሁሉ የተቻለውን ያህል አቅሙን ሳይቆጥብ በፍፁም በመንጠራራት የበኩሉን ጥረት ቢያደርግ ለውጥ ማየት እንቻል፤
- ጽ/ቤቱ ከ1999 ዓ.ም እና 200 ዓ.ም በተሻለ አዳዲስና ተጨማሪ የሥራ ዕቅዶችን በስፋት አቅዶ እና መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጡን ተግባራዊነት በኃላፊነት በማስተባበር እየተቀሳቀሰ ስለሆነ ለተግበራዊነቱ የሁሉም ዕገዛ ድጋፍና ተሣትፎ ሊታከልበት የሚገባ መሆኑ፤

የዕቃ ግዥ አፈፃፀም በጽ/ቤቱ ዕቅድ መሠረት ወቅትና ጥረት በጠበቀ ተፋጥኖ አለመቅረብ የታዩ ችግሮች ሲሆኑ ከምን ተገብረው መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ አንፃር የአሠራርና የአፈፃፀም ስልት የሚሻሻልበት መንገድ ቢቀየስ